

# ሊዲያ

- ጳውሎስና ሲላስ በሚጓዙበት ስፍራ ሁሉ ጢሞቴዎስ የሚባል አንድ ወጣት ሰባኪ አብሯቸው ይጓዝ ነበር።
  ጢሞቴስ በኢየሱስ የምታምን አይሁዳዊት እናት ስትኖረው አባቱ ደግሞ ግሪካዊ ነበር።

- በጉዟቸው መንፈስ ቅዱስ በአንድ ቦታ ያላቸውን ቆይታ ከፈፀሙ በኋላ ቀጥሎ የት መሄድ እንዳለባቸው ይነግራቸው ነበር።
  በጢሮአዳ በነበሩበት  አንድ ሌሊት ጳውሎስ አንድ ራዕይ አየ።  በዚህ ራዕይም አንድ የመቄዶንያ ሰው ወደመቄዶንያ መጥቶ እንዲረዳው ሲጠይቀው ያያል። አሁንም እንደገና መንፈስ ቅዱስ ምሪቱን እየሰጣቸው ነበር።

- ወዲያውኑም ለጉዞ ዝግጅት ጀመሩ። ከጢሮአዳ እስከ መቄዶንያ ድረስ በመርከብ ለመጓዝ ርቀት ነበረው። በጉዟቸውም ፊልጵስዩስ ደረሱ። ፊልጵስዩስ በመቄዶንያ ከሚገኙ ትልልቅ የሮም ግዛት ከተሞች አንደኛዋ ነበረች።

- በፊልጵስዩስ ለበርካታ ቀናት ቆይታ አደረጉ። በዚያ በነበሩበት ጊዜም በከተማይቱ ውስጥ በሰንበት እግዚአብሔርን ለማምለክ በወንዝ አጠገብ በሚገኝ የመሰብሰቢያ ስፍራ ይገናኙ ስለነበሩ ሰዎች  ሰሙ። በዚያም ተገኝተው ለፀሎት የተሰበሰቡትን ሴቶች መስበክ ጀመሩ።  ከእነኝህ ሴቶች መካከል አንደኛዋ ትያጥሮን ከምትባልና ከምስራቅ መቄዶንያ ከተማ የመጣች ሊዲያ የምትባል ሴት ነበረች።  እርሷም ከቀይ ሐር የተሰራ ልብስ በመሸጥ የምትተዳደር ሴት ነበረች።

- በዚያን ጊዜ ቀይ የሐር  ልብስ እጅግ በጣም ውድ ነበር። ውድ የሆነበት ምክንያትም ለመስራት በጣም ከባድ ስለሆነ ነበር። ለዚህ የቀይ ሐር ልብስ የሚያስፈልገው ቀለም የሚገኘው ከባህር ውስጥ ከሚገኝ ለየት ካለ የአሳ ዘር ነው። ከዚህ አሳ የሚገኘው ፈሳሽ ቀለሙ ነጭ ሲሆን በፀሐይ ላይ ትንሽ ሲቆይ ወደ ብሩህ ሐምራዊና ቀይ ቀለም ይቀየራል። ለእንደዚህ አይነቱ ቀለም የሚያስፈልጉ አሳዎችን መሰብሰብ ደግሞ አድካሚና አስቸጋሪ ስራ ነበር።

- እንዲህ አይነቱን ልብስ በዋነኝነት የሚለብሱት ደግሞ የንጉሳውያን ቤተሰቦችና የሮም ምክር ቤት አባላት ነበሩ። ጳውሎስ በሚሰብክበት ጊዜም እግዚአብሔር የሊዲያን ልብ ከፍቶ ስለኢየሱስ የሚሰበከውን ስብከት እንድትረዳ አደረገ። በስብከቱ አምና ምላሽ ሰጠች።  እርሷና መላ ቤተሰቧም ተጠመቁ።

- ጳውሎስንና ከእርሱ ጋር የነበሩትንም እርሷ በጌታ እንዳመነች ከተቀበሉ በቤቷ እንግድነት እንዲመጡ ጠየቀቻቸው። አራቱንም ማለትም ጳውሎስን፣ ሲላስን፣ ጢሞቴዎስንና ሉቃስን ለማስተናገድ በቂ ክፍሎች እንደሏት መገመት አይከብድም።  ልመናዋን ስላበረታችውም ከእርሷ ጋር ለመሄድ ተስማሙ።

- የሊዲያ ልብ ልክ በዘሪው ምሳሌ እንደተጠቀሰው እንደ መልካሙ መሬት ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰማ በደስታ ተቀብላ ታዘዘች።

*የሊዲያ ታሪክ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ 16፡ 1 – 15 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com